ተራጋሚዎች የትንሳኤ ቀን መስካሪዎችም ሆነ አማላጅ አይሆኑም።

ከአቡ ደርዳእ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "ተራጋሚዎች የትንሳኤ ቀን መስካሪዎችም ሆነ አማላጅ አይሆኑም።"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አላግባብ እርግማን የሚያበዛ ሰው ለሁለት ቅጣቶች እንደሚዳረግ ተናገሩ: የመጀመሪያው: የትንሳኤ ቀን መልክተኞች ለህዝቦቻቸው ተልእኳቸውን እንዳደረሱ ከሚመሰክሩ ምስክሮች አይሆኑም፤ አመፀኛ ስለሆነም በዱንያም ምስክርነቱ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ሰማዕትነትንም እርሱም በአላህ መንገድ መገደል ስለሆነ አይገጠምም። ሁለተኛው: አማኞች የትንሳኤ ቀን እሳት መግባት ግድ የሆነባቸውን ወንድሞቻቸውን በሚያማልዱበት ጊዜ እነርሱ ግን አያማልዱም።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5495